# ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
2015/23

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

## የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ለ63 ሴት ሥራ ፈጣሪዎች በወተት ምርትና በእንስሳት እርባታ ስኬታማ የሚያደርግ ሥልጠና ሰጠ

**አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ፤ሰኔ 12 ቀን 2007 ዓ.ም.፡-** የአሜሪካ መንግሥት በዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲው (USAID) በኩል 63 ሴቶችን በቴክኒክና በንግድ ሥራ ክህሎቶች አሠልጥኖ በዛሬው ዕለት አስመረቀ፡፡ ሠልጣኞቹ በሥልጠናው ወቅት በስኬታማ የወተት እና የሥጋ ምርት አቅርቦት፣እንዲሁም የቁም ከብት ንግድ ባለቤት መሆን በሚችሉበት ሁኔታ ዙሪያ ከፍተኛ ግንዛቤ ጨብጠዋል፡፡

ሥልጠናው የተዘጋጀው በ2004 ዓ.ም. በተደረገ ጥናት፤ ሴቶች በወተት ምርትና በእንስሳት እርባታው ዘርፍ በአመራር ዕውቀት፣በንግድ ሥራ አገልግሎቶች ተደራሽነት፣ውሳኔ በመስጠት፣በስኬታማ የንግድ ሥራ ዕቅድ አዘገጃጀት ረገድ ክፍተቶች እንዳሉባቸው በመጠቆሙ ነው፡፡

በጥናቱ በተጠቆሙ ክፍተቶች መሠረትም፤ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ በግብርና ዕድገት ፕሮግራም-የእንስሳት ገበያ ልማት እና ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ በሚያስችል አቅም መመረቅ በተሰኙ መርሀ ግብሮች በኩል በመጋቢት ወር 2007 ዓ.ም. የሥራ ፈጠራ አቅም አላቸው ተብለው ለተመረጡ ሴት ሥራ ፈጣሪዎች የአስተዳደርና የአመራር ሥልጠና እንዲሰጣቸው አድርጓል፡፡ እነዚህ ሴቶች በአስተዳደርና በሥራ አመራር ክህሎት ሥልጠና የተሰጣቸው ሲሆን፤ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያግዝ የንግድ ሥራ ዕቅድ በመንደፍ ረገድም የቴክኒክ ዕውቀት አግኝተዋል፡፡

63ቱ ተመራቂዎች የምግብ ዋስትና ችግር ካለባቸው ከአማራ፣ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም ከትግራይ ክልል ወረዳዎች የተውጣጡ ሲሆን፤በየአካባቢያቸው የተማሩትን ትምህርት ተጠቅመው ለሌሎች ሴቶች አርአያ ይሆናሉ፤ያሠለጥኗቸዋልም፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ተወካይ የሆኑት ካለን ሂዩስ ለተመራቂዎች ንግግር ባደረጉበት ወቅት፡-“ሴቶች በእንስሳት እርባታና በእንስሳት ምርት አያያዝ የሚጫወቱትን ሚና ማሳደግ በቤተሰብም ሆነ በሀገር ደረጃ ከፍ ያለ ጠቀሜታ አለው፡፡ በንግድ ሥራ አስተዳዳርና አመራር ላይ ያተኮረው ይህ ሥልጠና በእንስሳት እርባታ እምቅ አቅም ያላቸው አርአያ ሴቶች ላይ ማተኮሩ ሴቶች በዚህ ሥልጠና በመስኩ የመሪነቱን ሚና እንዲጫወቱ ያደርጋቸዋል፤በየአካባቢያቸው ላሉ ሴቶችም አርአያ በመሆን ያሠለጥኗቸዋል ተብሎ በመታመኑ ነው” ብለዋል፡፡

መጪውን ትውልድ መመገብ በተሰኘ የአሜሪካ መንግሥት ውጥን ሥር የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ የሥራ ፈጠራ እምቅ አቅም ያላቸውን ሴቶች መርጦ በማሠልጠንና

በማብቃት፣እንዲሁም ለሌሎች አርአያ እንዲሆኑ በማድረግ የወተት ምርትና የእንስሳት እርባታውን ዘርፍ ያሻሽላል፤ምርታማነቱንና ተወዳዳሪነቱንም ያሳድጋል።

###